## የዲጂታል ሽግግር

*[የዲጂታል ቲቪ (ዲቲቪ) ሽግግር ምንድን ነው።]*

*ወደ ዲቲቪ መሸጋገሩ ለምን አስፈለገ?*

*ዲቲቪ ለመከታተል እስከ ፈብሯሪ 17/2009 መጠበቅ ይኖርብኛል?*

*ለአናሎግ ቲቪ ስርጭት ማብቂያ ዝግጁ ለመሆን ምን ያስፈልገኛል?*

*አናሎግ ቴሌቪዥኔን ከፈብሩዋሪ 17/2009 በኋላ ማስወገድ ይኖርብኛል ማለት ነው።*

*የሙሉ ኃይል አናሎግ ቴሌቪዥን ስርጭት የሚያበቃበት ፈብሯሪ 17/2009 ሊራዘም ይችላል?*

## ቴሌቪዥንዎ

*አዲስ ቴሌቪዥን መግዛትና ከሽግግሩ በኋላ የዲጂታል ቴሌቪዥን ስርጭትን መከታተል ከፈለግኩ ሀይ ዴፈኒሽን ቲቪ (ኤችዲቲቪ) መግዛት ይኖርብኛል።*

*ዲጂታል ቴሌቪዥን (ዲቲቪ) ስለመግዛቴ እንዴት ርግጠኛ መሆን እችላለሁ።*

*ያለኝ ቲቪ ደጂታል ቲቪ ይሆን እንደሆን እንዴት ላውቅ እችላለሁ ?*

*በ‹‹ኢንቴግሬትድ›› ዲቲቪዎች እና በዲቲቪ ወይም ኤችዲቲቪ ‹‹ማሳያዎች›› መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?*

*የቪዲዮ ካሴት ማጫወቻዬን፣ ዲቪዲ ማጫወቻዬን እና የጨዋታ መሣሪያዬን በዲጂታል ቴሌቪዥን ላይ መጠቀም እችላለሁ?*

*የዲቲቪ ወይም ኤችዲቲቪ ፕሮግራምን እንዴት አገኛለሁ?*

*ምድር ለምድር የሚሰራጭ ዲቲቪ ለመቀበል ልዩ አንቴና ያስፈልገኛል?*

*በዲቲቪዎች የሚተኩት የቀድሞ አናሎግ ቲቪዎች መጨረሻ ምንድን ነው? ሪሳይክል ማድረግ የሚቻልበት መንገድ አሉ?*

## ኬብል እና ሣተላይት

*በዲቲቪ ሽግግሩ የኬብል አገልግሎቶችን በሚጠቀሙ ቲቪዎች ላይ ተጽዕኖ አለው?*

*የኬብል አገልግሎት የሚሰጠኝ ኩባንያ አሁን ያለ ሣጥን የምቀበላቸውን የኬብል ቻነሎች ለመቀበል ሣጥን እንዲኖረኝ ሊያደርግ ይችላል?*

*ኤፍሲሲ የኬብል ኩባንያዎች አገልግሎታቸውን ወደ ዲጂታል እንዲቀይሩ ያደርጋል?*

*ዲጂታል ፕሮግራሞችን ከኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ማግኘት ችዬ እንደሆን እንዴት አውቃለሁ?*

*የኬብል አገልግሎት አቅራቢዬ የዲጂታል ኬብል ፓኬጅ ያቀርባል። ይህ ከኤችዲቲቪ ጋር ተመሣሣይ ነው?*

*እንደ ሲኤንኤን፣ ኤምኤስኤንቢሲ፣ ላይፍታይም ወዘተ ያሉ የኬብል ቲቪ ኔትወርኮች ወደ ዲጂታል ስርጭት መቀየር አለባቸው?*

*አናሎግ ቴሌቪዥኖች ያሏቸው የኬብል አገልግሎት ደንበኞች የሴት- ቶፕ ሳጥንን ከኬብል ኩባንያቸው መግዛት ወይም መከራየት ይኖርባቸዋል; ይህ ከሆነ ዋጋው ምን ያህል ነው።*

*የዲቲቪ ሽግግሩ የሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ቲቪዎች ተጽዕኖ አለው።*

## ቀያሪ ሳጥን

*የቀያሪ ሳጥን ኩፖን ፕሮግራም ምንድን ነው?*

*ለኩፖን ብቁ የሆኑ ከዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች የትኞቹ ናቸው?*

*በአንድ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ላይ ከአንድ በላይ ቲቪ እና ቪዲዮ ሪከርደር ማገናኘት እችላለሁ?*

*ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች (የምድር ለምድር የቲቪ ስርጭቶችን ቀይረው በአናሎግ ቲቪ እንዲታዩ ማድረግ የሚችሉ) ዲጂታል ክሎዝድ ካፕሽኒንግን መቀየር ይችላሉ?*

*ከቴሌቪዥኔ ጋር በሁለት ሽቦዎች የተገናኘ የቀድሞ አንቴና አለኝ። በዚህ አንቴና አማካኝነት የመቀየሪያ ሳጥን መጠቀም እችላለሁ?*

## ጠቅላላ ጥያቄዎች

*ተንቀሳቃሹን በባትሪ ኃይል የሚሰራውን ቴሌቪዥኔን ከፌብሯሪ 17/2009 ዘጠኝ በኋላ የቴሌቪዥን ስርጭትን ልከታተልበት እችላለሁ?*

*በአናሎግ ቲቪዬ ላይ ያለው የኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ መስራቱን ይቀጥላል?*

*ራዲዮኔ አሁኑ ወቅት የቲቪ ቻነሎችን የድምጽ ክፍል ይቀበላል። ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ መሥራቱን ይቀጥላል?*

*በአካባቢዬ የሚገኘው የኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ ጣቢያ የቲቪ ቻነልን የድምጽ ክፍል መልሶ ያሰራጫል። የራዲዮ ጣቢያው ይህን አገልግሎቱን ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ ይቀጥላል?*

*በአካባቢዬ የሚገኝ የቴሌቪዥን ጣቢያ የኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ ጣቢያዎችን በቴሌቪዥን ቻነል መልሶ ያስተላልፋል። ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ እነዚህን ተመልሰው የሚሰራጩ የራዲዮ ሥርጭቶች በቴሌቪዥኔ ማድመጥ እችላለሁ?*

*ዲጂታል የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያዎችን መስጠታቸውን ይቀጥላሉ?*

*[የአነስተኛ ኃይል (ኤልፒቲቪ)፣ ምድብ ሀ እና ቲቪ ትራንስሌተር  ጣቢያዎች ምንድን ናቸው? የዲቲቪ ሽግግር ተጽዕኖ የሚያሳድርባቸው በምን መልኩ ነው?]*

*[ከዲጂታል ሽግግሩ በኋላ ከኤልፒቲቪ ወይም ከትራንስሌተር ጣቢያዎች የምድር ለምድር አናሎግ የቲቪ ሥርጭቶችን ለመከታተል ያሉኝ አማራጮች ምንድን ናቸው?]*

*[እንደ  ቪ-ቺፕ ያሉ የወላጅ መቆጣጠሪያዎችን አሁን በአናሎግ ቲቪዬ ላይ እንደምጠቀመው  ሁሉ በዲጂታል ቲቪም መጠቀም እችላለሁ?]*

*[በዲጂታል ቴሌቪዥኔ ላይ የምመለከተው ምስል የቲቪውን ስክሪን ሙሉ በሙሉ የማይሸፍ ነው ለምንድን ነው?]*

*[በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ ከምስሉ አናት እና ግርጌ ላይ ያሉት ጥቁር መስመሮች ለምን ይፈጠራሉ?]*

*[አንዳንድ በዲጂታል ቴሌቭዥኔ የምመለከታቸው ፕሮግራሞች ከሌሎች ይበልጥ ‹ጥራት ያላቸው› ለምንድን ነው?]*

---

## ደጂታል ሽግግር

### የዲጂታል ቲቪ (ዲቲቪ) ሽግግር ምንድን ነው?

የቴሌቪዥን ስርጭት ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የሚቀርበት ሂደት የዲጂታል ቲቪ (ዲቲቪ) ሽግግር ተብሎ ይጠራል፡፡ በ1996 የዩ.ኤስ. ኮንግረስ ተጨማሪ የስርጭት ቻነሎችን ለእናንዳንዱ የቲቪ ጣቢያ እንዲሰጥና በዚህም የቲቪ ጣቢያዎቹ ከአናሎግ ስርጭት ቻነሎቻቸው በተጓዳኝ የዲጂታል ስርጭት ቻነል መጠቀም እንዲችሉ ፈቃድ ሰጥቷል፡፡ ኋላ ላይም ኮንግረሱ ጣቢያዎቹ እስከ ፌብሯሪ 17/2009 ድረስ ብቻ በአናሎግ እንዲያሰራጩ ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡ በዩ.ኤስ. ገበያ ውስጥ ያሉ ማሰረጫ ጣቢያዎች በአሁኑ ወቅት በአናሎግና በዲጂታል መንገድ በማሰራጨት ላይ ናቸው፡፡ ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ የሙሉ ኃይል ቴሌቪዥን ጣቢያዎች በዲጂታል ብቻ ያስራጫሉ፡፡

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

### ወደ ዲቲቪ መሸጋገሩ ለምን አስፈለገ?

ወደ ሙሉ ዲጂታል ስርጭት የመሸጋገሩ ሁኔታ ለሕዝብ ደህንነት ግንኙነቶች (ለፖሊስ፣ ለእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንቶችና ለነፍስ አድን ቡድኖች) መገልገያነት ሊውሉ የሚችሉና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የስርጭት ክልሎች ከመጨናነቅ ነጻ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተጨማሪም የተወሰነው የማሰራጫ ክፍል የረቀቁ ሽቦ አልባ አገልግሎቶችን (ሽቦ አልባ ብሮድባንድ የመሳሰሉትን) ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ለሚችሉ ኩባንያዎች መጠቀሚያነት በጨረታ ይሰጣል፡፡

ዲጂታል ስርጭቱ ጣቢያዎች የተሻለ የምስልና የድምጽ ጥራትን እንዲያሠራጩ የሚያስችሉ በመሆኑ እንዲሁም ዲጂታል ከአናሎግ የተሻለ ብቃት ያለው በመሆኑ ተጠቃሚዎችም ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ለምሣሌ አንድ ማሰራጫ በአንድ የአናሎግ ፕሮግራም ላይ ከመወሰን ይልቅ ‹‹መልቲ ካስቲንግ›› በተባለ ሂደት አማካኝነት የከፍተኛ ጥራት ‹‹ሀይ ዴፊኒሽን›› (ኤችዲ) ዲጂታል ፕሮግራምን ወይም በርካታ የ‹‹ስታንዳርድ ዴፊኒሽን›› (ኤስዲ) ዲጂታል ፕሮግራሞችን በአንድ ጊዜ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡ የመልቲ ካስቲንግ ዘዴ ማሰራጫ ጣቢያዎች አንድ የአናሎግ ፕሮግራምን ለማሰራጨት የሚያስችል የማሰራጫ ክልልን በመጠቀም በርካታ የዲጂታል ፕሮግራም ቻነሎችን በአንድ ጊዜ ለማስተላለፍ ያስችላቸዋል፡፡

በመሆኑም ለምሣሌ በቻነል 7 ላይ በአናሎግ የሚያሰራጭ ጣቢያ አንድ ፕሮግራም ብቻ ለተመልካቾች ማቅረብ የሚችል ሲሆን፤ በአንጻሩ በቻነል 7 ላይ በዲጂታል የሚያሰራጭ ጣቢያ በቻነል 7-1 ላይ አንድ ዲጂታል ፕሮግራም፣ በቻነል 7-2 ላይ ሌላ ሁለተኛ ፕሮግራም፣ በቻነል 7-3 ላይ ሦስተኛ ፕሮግራም፣ በሌሎቹም ላይ በዚህ መልኩ ለተመልካቾች ማሰራጨት ይችላል። ይህም ተመልካቾች ሰፊ የፕሮግራም አማራጮች እንዲኖራቸው ያደርጋል ማለት ነው።

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**ለአናሎግ ቲቪ ስርጭት ማብቂያ ዝግጁ ለመሆን ምን ያስፈልገኛል?**

*ኮንግረሱ የሙሉ ኃይል ቴሌቪዥን ጣቢያዎች እስከ ፌብሯሪ 17/2009 ድረስ ብቻ በአናሎግ እንዲያሰራጩ ያዘዘ በመሆኑ ከዚያ ቀን በኋላ የምድር ለምድር የቲቪ ስርጭቶች ዲጂታል ብቻ ይሆናሉ። ነጻ የምድር ለምድር የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን የሚቀበሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቴሌቪዥኖች ካሉዎት (የጣሪያ ላይ ወይም በቲቪው ላይ የሚቀመጥ ‹‹የጥንቸል ጆሮ›› የመሠለ አንቴና አማካኝነት)፤ በዚሁ ቴሌቪዥን የቴሌቪዥን ስርጭቶችን መቀበል ከመቻልዎ በፊት ከዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ያስፈልግዎታል። ሣጥኑ አካባቢዎ ከሚገኙ ጣቢያዎች የሚተላለፍን ማንኛውንም ዓይነት ተጨማሪ የመልቲካስት ፕሮግራም እንደመለከቱ ያስችልዎታል።*

*በዲቲቪ ሽግግር ወቅት ተጠቃሚዎችን ለወርዳት መንግሥት ዲጂታል-ወደ-አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን የኩፖን ፕሮግራምን ነጽፏል። የንግድ ዲፖርትመንት አካል የሆነው ብሔራዊ የቴሌከምዩኒኬሽን እና መረጃ አስተዳደር (ኤንቲአይኤ) ይህን ፕሮግራም ይመራል። እያንዳንዱ በዩ.ኤስ. የሚገኝ ቤተሰብ ብቁ የሆኑ ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖችን መግዛት ይችል ዘንድ እያንዳንዳቸው 40 ዶላር ዋጋ ያላቸውንና እስከ ሁለት የሚደርሱ ኩፖኖችን ማግኘት ይችላል። ኤንቲአይኤ ከጃንዋሪ 2008 ጀምሮ ለኩፖን የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል ጀምሯል። ኩፖኖቹ ተሣታፊ በሆኑ የተጠቃሚ ኤሌክትሮኒክስ ችርቻሮ ነጋዴዎች ዘንድ የሚሸጡ ብቁ ቀያሪ ሳጥኖችን ለመግዛት ብቻ የሚያስችሉ ሲሆን ኩፖኖቹ አገልግሎት ላይ መዋል ያለባቸው በግዢው ወቅት ብቻ መሆን አለበት (ኩፖኖቹ ከተላኩ ከ90 ቀናት በኋላ ዋጋቸውን እንደሚያጡ ልብ ይበሉ)። በአምራቾች ግምት መሠረት ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች እያንዳንዳቸው ከ40 እስከ 70 ዶላር ይሸጣሉ፤ ይህም የአንድ ጊዜ ወጪ ነው። በዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን የኩፖን ፕሮግራም ዙሪያ ተጨማሪ መረጃዎችን ከwww.dtv2009.gov ድረ ገጽ ወይም በስ.ቁ 1-888-388-2009 (የድምጽ ጥሪ) አሊያም በ1-877-530-2634 (ቲቲዋይ) ደውለው ማግኘት ይችላሉ።*

*ከኬብል ወይም ከሣተላይት አገልግሎት ጋር የተገናኘ ቴሌቪዥን ያላቸው የኬብል እና የሳተላይት ቲቪ ደንበኞች በፌብሯሪ 17/2009 የሚያበቃው የሙሉ ኃይል አናሎግ ስርጭት ማብቂያ ቀን አይመለከታቸውም።*

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**ዲቲቪ ለመከታተል እስከ ፌብሯሪ 17/2009 መጠበቅ ይኖርብኛል?**

በአሁኑ ወቅት ዲጂታል የቴሌቪዥን ስርጭት የለም። አሁን የምድር ለምድር የቴሌቪዥን ስርጭቶችን መከታተል ከቻሉና የዲቲቪ መቀበያ ካለዎት አካባቢዎ ከሚገኙ ጣቢያዎች የሚተላለፉ ዲጂታል ሞገዶችን በሙሉ አሊያም አብዛኞቹን መቀበል መቻል ይኖርብዎታል። ከአካባቢዎ ጣቢያዎች የሚተላለፉ የሀይ ዴፊኒሽን እና መልቲካስት ፕሮግራሞችን ሊመለከቱም ይችላሉ። አሁን ስላሉት ዲጂታል ቴሌቪዥኖች ይበልጥ ለማወቅ የአካባቢዎን ፕሮግራሞች ዝርዝር ይመልከቱ ወይም ከአካባቢዎ ቲቪ ጣቢያዎች ጋር ይገናኙ። በዲጂታል ቴሌቪዥን ዙሪያ ተጨማሪ መረጃዎችን ከኤፍሲሲ ልዩ ድረ ገጽ www.dtv.gov ማግኘት ወይም በስ.ቁ. 1-888-225-5322 (ቲቲዋይ 1-888-835-5322) መደወል ይችላሉ።

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**የሙሉ ኃይል አናሎግ ቴሌቪዥን ስርጭት የሚያበቃበት ፌብሯሪ 17/2009 ሊራዘም ይችላል?**

ፌብሯሪ 17/2009 የሙሉ ኃይል አናሎግ ቴሌቪዥን ስርጭት የሚያበቃበት የመጨረሻው ቀን መሆኑ በፌደራሉ ሕግ ተደንግጓል። ቀነ ገደቡ እንዲሟላ ለማድረግና የሙሉ አቅም አናሎግ ቴሌቪዥን ስርጭት ለሚያበቃበት ቀን ሁሉም ሰው ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥ የመንግስት ኤጀንሲዎች፣ ኢንደስትሪዎች፣ የሕዝብ ፍላጎት ጠባቂ ቡድኖች እና ሌሎችም ጉዳዩ ይመለከተናል የሚሉ ድርጅቶች ጠንክረው በመሥራት ላይ ናቸው።

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**የቀድሞውን አናሎግ ቴሌቭዥኔን ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ ማስወገድ ይኖርብኛል?**

አይኖርብዎትም። ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥንን በመጠቀም የአሁኖቹን የምድር ለምድር ዲጂታል ስርጭቶች በአናሎግ ቴሌቪዥንዎ መከታተል ይችላሉ። ያለዎትን አናሎግ ቴሌቪዥን ማስወገድ አያስፈልግዎትም። በተጨማሪም አናሎግ ቴሌቪዥኖች እንደ ኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ ያሉ በደንበኝነት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመጠቀም ያስችላሉ። በተጨማሪም አሁን የሚጠቀሙባቸውን የጨዋታ ዕቃዎች፣ የቪዲዮ ካሴት ሪከርደሮች፣ ዲቪዲ ማጫወቻዎችና ተመሣሣይ ምርቶችን መጠቀምዎን መቀጠል ይችላሉ።

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**ቴሌቪዥንዎ**

**አዲስ ቴሌቪዥን መግዛትና ከሽግግሩ በኋላ የዲጂታል ቴሌቪዥን ስርጭትን መከታተል ከፈለግኩ ሀይ ዴፊኒሽን ቲቪ (ኤችዲቲቪ) መግዛት ይኖርብኛል።**

አይኖርብዎትም። የዲቲቪ ሽግግሩ ከአናሎግ ስርጭት ወደ ዲጂታል ስርጭት የሚደረግ ሽግግር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ከአናሎግ ስርጭት ወደ ሀይ ዴፊኒሽን ስርጭት የሚደረግ ሽግግር አይደለም። ዲጂታል ስርጭት የሀይ ዴፊኒሽን ስርጭት ለማካሄድ የሚያስችል ቢሆንም ሀይ ዴፊኒሽን ግን አስፈላጊ አይሆንም። እርስዎም ዲጂታል ቴሌቪዥንን ለመከታተል ኤችዲቲቪ መግዛት አያስፈልግዎትም። ምድር ለምድር የሚሰራጩ የቴሌቪዥን ስርጭቶችን ለመከታተል የሚያስፈልግዎ ስታንዳርድ ዴፊኒሽን ዲቲቪ (ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ አብሮ የተሠራለት ቲቪ) አሊያም ከዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ጋር የተገኘና አናሎግ ቴሌቪዥን ብቻ ነው። የዲጂታል ስርጭት ቴሌቪዥን፤ የስታንዳርድ ዴፊኒሽን (ኤስዲ) እና ሀይ ዴፊኒሽን (ኤችዲ) ፎርማቶችን ያካትታል።

የሀይ ዴፊኒሽን ፕሮግራሞችን በስታንዳርድ ዴፊኒሽን ዲቲቪ ወይም ከዲጂታል ወደ አናሎግ ከሚቀይር ሳጥን ጋር በተገናኘ አናሎግ ቲቪ መመልከት የሚችሉ ሲሆን ጥራቱ ግን እንደ ሀይ ዴፊኒሽን አይሆንም። የስታንዳርድ ዴፊኒሽን ዲቲቪዎች ዋጋ ተመሣሣይ መጠን ካለው አናሎግ ቴሌቪዥን ዋጋ ጋር ተቀራራቢ ነው።

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**ዲጂታል ቴሌቪዥን (ዲቲቪ) ስለመግዛቴ እንዴት ርግጠኛ መሆን እችላለሁ።**

ከማርች 1/2007 አንስቶ ወደ ዩ.ኤስ. የሚገቡ ወይም በግዛቶች መካከል በሚደረግ ንግድ የሚተላለፉ የቴሌቪዥን ስርጭት መቀበያ መሣሪያዎች በሙሉ (ቲቪዎችን፣ ቪዲዮ ካሴት ሪከርደሮችን፣ ዲቪአሮችን ወዘተ ጨምሮ) ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ያላቸው መሆን እንደሚገባቸው በሕግ ተደንግጓል። ሻጮች አናሎግ ብቻ ሆኑ ቴሌቪዥኖችን ከመጋዘናቸው መሸጣቸውን መቀጠል የሚችሉ ቢሆንም፣ የሚከተለውን መልዕክት የያዘ የተጠቃሚዎች ማስጠንቀቂያ ሌብል አናሎግ ብቻ በሆነው መሣሪያ ላይ ወይም አጠገብ በግልጽ በሚታይ መልኩ ማኖር አለባቸው።

## ማስጠንቀቂያ ለደንበኛው

**ይህ የቴሌቪዥን መቀበያ የአናሎግ ስርጭት ጣቢያ መቀበያ ብቻ ያለው በመሆኑ ከፌብሯሪ 17/2009 ጀምሮ የሚተላለፉ የምድር ለምድር ስርጭቶችን በአንቴና ለመቀበል የመቀየሪያ ሳጥን ያስፈልገዋል፡፡ ይህም መንግሥት ባደረገው ወደ ዲጂታል ስርጭት የመሸጋገር ሂደት ምክንያት ነው፡፡ አናሎግ ብቻ የሆኑ ቲቪዎች እንደ ቀድሞው ለኬብልና ለሳተላይት ቲቪ አገልግሎቶች፣ ለጨዋታ መሣሪያዎች፣ ለቪዲዮ ካሴት ሪከርደሮች፣ ለዲቪዲ ማጫወቻዎችና ለተመሳሳይ ምርቶች ማገልገል ይኖርባቸዋል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ የፌዴራል ኮምዩኒኬሽንስ ኮሚሽንን በስ.ቁ. 1-888-225 5322 (ቲቲዋይ 1-888-835-5322) ደውለው ማግኘት አለያም የኮሚሽኑን የዲጂታል ቴሌቪዥን ድረ ገጽ www.dtv.gov መጎብኘት ይችላሉ፡፡**

በመሆኑም ለሽያጭ የሚቀርቡ የቴሌቪዥን መሣሪያዎች በሙሉ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ሊኖራቸው ወይም የጣቢያ መቀበያ የሌላቸው መሆኑ በሚሸጡበት ሥፍራ ላይ ሊገለጽ ይገባል፡፡ አዲስ ቲቪ ወይም የቲቪ መሣሪያ በሚገዙበት ወቅት ይህን መለያ ምልክትና አናሎግ ብቻ የሆኑ መሣሪያዎችን አሉታዊ ጎን ግምት ውስጥ ማስገባት አይዘንጉ፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**ያለኝ ቲቪ ደጂታል ቲቪ ይሆን እንደሆን እንዴት ሳውቅ እችላለሁ ?**

ብዙ ዲቲቪዎችና የዲጂታል ቴሌቪዥን መሣሪያዎች ዲጂታል ጣቢያ መቀበያዎች ያሏቸው መሆኑን የሚያሳዩ ሌብሎች ወይም ምልክቶች ይደረጉባቸዋል፡፡ ወይም አብረዋቸው በመጡ የመረጃ ማቴሪያሎች ላይ መግለጫዎች ይጻፋሉ፡፡ በእነዚህ ምልክቶች ላይ ከሚስፍሩት ቃላት መካከል ‹‹ኢንቴግሬትድ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ››፣ ‹‹አብሮ የተሠራ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ›› ወይም ‹‹ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ›› ‹‹ዲቲቪ›› ‹‹ኤቲኤስሲ›› ወይም ‹‹ኤችዲቲቪ›› (ሀይ ዴፊኒሽን ቴሌቪዥን)፡፡ የቴሌቪዥን መሣሪያዎት ከእነዚህ ሌብሎች ወይም ምልክቶች ውስጥ ማናቸውም ካሉበት፤ ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን መጠቀም ሳያስፈልግዎት ምድር ለምድር የሚሠራጩ ዲጂታል ፕሮግራሞችን መመልከት መቻል ይኖርብዎታል (ያስታውሱ ነጻ የምድር ለምድር ዲጂታል ፕሮግራሞችን ለመመልከት ኤችዲቲቪ አያስፈልግዎትም፡፡ ቴሌቪዥንዎ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ እስካለው ድረስ ምድር ለምድር የሚሠራጩ ዲጂታል ስርጭቶችን መመልከት ይችላሉ፡፡ ኤችዲቲቪ የሚያስፈልግዎት የሀይ ዴፊኒሽን ፕሮግራሞችን በተሟላ የኤችዲ ጥራት መመልከት ከፈለጉ ብቻ ነው)፡፡ በተጨማሪም ከቴሌቪዥን መሣሪያዎት ጋር አብሮ የመጣውን የአጠቃቀም መመሪያ ወይም ሌላ ማንኛውንም ማቴሪያል ተጠቅመው ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

ቴሌቪዥንዎ ላይ ‹‹ዲጂታል ማሳያ›› ወይም ‹‹ኤችዲቲቪ ማሳያ›› ወይም ‹‹ለዲጂታል ዝግጁ›› ወይም ‹‹ለኤችዲቲቪ ዝግጁ›› የሚል ጽሑፍ ቢኖርበት ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ አለው ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም ምድር ለምድር የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን ለመመልከት ራሱን የቻለ ባለ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ሴት-ቶፕ ሳጥን ያስፈልግዎታል፡፡

ለዲጂታል ወይም ኤችዲ ‹‹ማሳያዎች›› የሚያገለግሉ የምድር ለምድር ዲጂታል ሴት-ቶፕ ሳጥኖችን ከችርቻሮ መደብሮች መግዛት ይችላሉ፡፡ የኬብልና የሳተላይት ቲቪ አቅራቢዎችም የሴት-ቶፕ ሳጥኖችን ለየራሳቸው አገልግሎት ይሸጣሉ ወይም ያከራያሉ፡፡

(ማሳሰቢያ፡- እዚህ ውስጥ የተጠቀሰው የዲጂታል ሴት-ቶፕ ሳጥን ከላይ ከተጠቀሰውና ነጻ የምድር ለምድር ዲጂታል ስርጭቶችን በአናሎግ ቲቪ ለማየት ከሚያስችለው ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን የተለየ ነው)፡፡

ቴሌቪዥንዎ ‹‹አናሎግ›› ወይም ‹‹ኤንቲኤስሲ›› የሚል ሌብል ካለበትና ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ እንዳለው የሚያመለክት ሌብል ከሌለበት አናሎግ ጣቢያ መቀበያ ብቻ አለው ማለት ነው፡፡

ቴሌቪዥንዎ ‹‹አናሎግ›› ወይም ሌላ የቴሌቪዥን መሣሪያዎ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ይኖረው ወይም አይኖረው እንደሆን ማወቅ ካልቻሉ የአምራቹን ስምና የሞዴሉን ቁጥር በመለየትና ከደንበኞች የኤሌክትሮኒክስ ነጋዴ ጋር በመገናኘት ቲቪው ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ያለው ወይ የሌለው መሆኑን እንዲያረጋግጡ ይመከራል፡፡ ይህን መረጃ አአምራቹ ድረ ገጽ ማግኘት የሚችሉበት ዕድልም አለ፡፡

በርካታ በዩ.ኤስ. ገበያ ውስጥ የተሰማሩ ማሰራጫ ጣቢያዎች በዲጂል እያሰራጩ የሚገኙ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ተጠቃሚዎች ዲቲቪን መከታተል ይችላሉ ማሰራጫ ጣቢያዎቹ በአሁኑ ወቅት ዲጂታል ፕሮግራማቸውን የሚያስራጩባቸውን የቻነል ቁጥሮች ለማወቅ የአካባቢዎን ማሰራጫ ጣቢያዎች ማግኘት ይችላሉ፡፡ ከዚያም ቴሌቪዥንዎ የምድር ለምድር ፕሮግራሞችን ለመቀበል በሚያስችል መልኩ መስተካከሉን (እንደ ኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ካሉ በክፍያ የሚሠሩ አቅራቢዎች ጋር ከመገናኘት በተለየ መልኩ) ማረጋገጥና የጣቢያ መፈለጊያዎን ምድር ለምድር በሚሰራጩ ቻንሎች ላይ በማድረግ የዲጂታል ስርጭት ፕሮግራምን መቀበል ይችሉ እንደሆነ ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**በ‹‹ኢንቴግሬትድ›› ዲቲቪዎች እና በዲቲቪ ወይም ኤችዲቲቪ ‹‹ማሳያዎች›› መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

ኢንቴግሬትድ ዲቲቪ የሚባለው አብሮ የተሰራ ዲጂል ጣቢያ መቀበያ ያለው ቴሌቪዥን ነው (በተጨማሪም ‹‹ዲቲቪ›› ተብሎ ይጠራል)፡፡ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ አንዳንዴ ዲቲቪ ካለዎት ምድር ለምድር የሚሰራጩ ዲጂታል ፕሮግራሞችን ለመቀበል ከመቀበያ አንቴና (የጣሪያ ላይ ወይም በቲቪው ላይ ከሚገጠም ‹‹የጥንቸል ጆሮ›› መሰል አንቴና) በስተቀር ተጨማሪ መሣሪያ አያስፈልግዎትም፡፡ ኢንቴግሬትድ ዲቲቪዎች የአናሎግ ስርጭት ፕሮግራሞችንም መቀበል የሚችሉ በመሆናቸው አናሎግ ስርጭቶችን መከታተልዎን መቀጠል ይችላሉ፡፡

በተቃራኒው የዲቲቪ ማሳያ ያለ ተጨማሪ መሣሪያ የዲጂታል ስርጭት ፕሮግራሞችን መቀበል አይችልም፡፡ የዲቲቪ ሞገድን ማቀነባበር የማይችል ተራ የማሳያ መሣሪያ ነው፡፡ ምድር ለምድር የሚሰራጩ ዲጂታል ወይም ኤችዲ ፕሮግራሞችን ለመቀበልና ለማሳየት ዲጂታል ወይም ኤችዲ ሴት-ቶፕ ሳጥን በአንቴናውና በማሳያው መካከል መገናኘት ይኖርበታል፡፡

ዲጂታል ወይም ኤችዲ ‹‹ማሳያ›› ካለዎትና ዲጂታል ወይም ኤችዲ ሴት-ቶፕ ሳጥን ገዝተው ምድር ለምድር የሚሰራጩ ፕሮግራሞችን ማየት ከፈለጉ የሴት-ቶፕ ሳጥኑ ከማሳያዎ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ከሻጩ ዘንድ ያረጋግጡ፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**የቪዲዮ ካሴት ማጫወቻዬን፣ ዲቪዲ ማጫወቻዬን እና የጨዋታ መሣሪያዬን በዲጂታል ቴሌቪዥን ላይ መጠቀም እችላለሁ?**

አዎ፡፡ ዲጂታል ቴሌቪዥኖች ‹‹ለቀድሞ መሣሪያዎች ተስማሚ›› ናቸው፤ ማለትም ያሉት አናሎግ መሣሪያዎች (ቪዲዮ ካሴት ሪከርደሮች፣ ዲቪዲ ማጫወቻዎች፣ ካምኮደሮች፣ የቪዲዮ ጌሞች ወዘተ) በዲጂታል ቴሌቪዥኖች ላይ ይሠራሉ፡፡ ሆኖም የምስል ጥራታቸው እያንዳንዱ መሣሪያ ባለው ከፍተኛ ሪዞሉሹን ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ አናሎግ መሣሪያዎች በዲቲቪዎች ላይ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት የሚኖራቸውን የምስልና ድምጽ ጥራት ለማሳደግ አምራቾች መሣሪያዎችን አንድ ላይ ለማገኘት የሚያስችሉ በርካታና የተለያዩ መገናኛዎችን በማምረት ላይ ናቸው በመሣሪያዎት ላይ ሊሰራ የሚችለውን የመገናኛ ዓይነት ለማወቅ በመሣሪያዎት ሻጭ ጋር ይገናኙ፡፡

[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]

**የዲቲቪ ወይም ኤችዲቲቪ ፕሮግራምን እንዴት አገኛለሁ?**

ምድር ለምድር የሚሠራጩ ዲጂታል ፕሮግራሞችን ለመቀበል (እንደ ኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ካሉ ክፍያን በሚጠይቁ አቅራቢዎች ከሚቀርቡ ዲጂታል ፕሮግራሞች በተቃራኒው) የሚከተሉት ያስፈልጉዎታል፡- (1) ዲቲቪ (ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ያለው ቲቪ) ወይም ዲጂታል-ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ጋር የተገናኘ አናሎግ ቲቪ እና (2) የስርጭት መቀበያ አንቴና (የጣቢያ አንቴና ወይም የ‹‹ጥንቸል ጆሮ››የመሰለ አንቴና ሆኖ ከቲቪዎች ጋር የተገናኘ)፡፡ በአጠቃላይ ምድር ለምድር የሚሠራጩ የአናሎግ ቲቪ ሞገዶችን በጥሩ ጥራት የሚቀበል አንቴና ለዲጂታል ቲቪ ስርጭት መቀበያነትም ማገልገል ይችላል፡፡

ዲጂታልፕሮግራሞችን የሚያሰራጩ የዩ.ኤስ. ቲቪ ጣቢያዎችን ዝርዝር ከhttp://www.fcc.gov/mb/video/files/dtvonair.html ማግኘት ይችላል፡፡ የሳተላይት ቲቪ አቅራቢዎችና በርካታ የኬብል ሲስተሞች በአሁኑ ወቅት የዲጂታል ፕሮግራሞችን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡ ደንበኞች በአካባቢያቸው ስለሚገኙ ዲጂታል ፕሮግራሞች ለማወቅ ከአገልግሎት አቅራቢዎች ጋር መገናኘት ይችላሉ፡፡

[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]

**ምድር ለምድር የሚሰራጭ ዲቲቪ ለመቀበል ልዩ አንቴና ያስፈልገኛል?**

በአጠቃላይ ሲታይ አስተማማኝ የምድር ለምድር ዲጂታል ፕሮግራም ስርጭት ቅበላ ለማድረግ አሁን የአናሎግ ቲቪ ፕሮግራሞችን በጥሩ ሁኔታ መቀበል ከሚችል የሞገድ መቀበያ መሣሪያ የተለየ መሣሪያ አያስፈልግም፡፡ አናሎግ የቲቪ ስርጭቶችን ለመቀበል የጣሪያ ላይ አንቴና ካስፈለገዎት የዲጂታል ቲቪ ስርጭቶችንም ለመቀበል ይኸው አንቴና በቂ ነው፡፡ ‹‹ለዲጂታል ዝግጁ›› ወይም ‹‹ለኤችዲ ዝግጁ›› የሚል ምልክት የሰፈረባቸውን አዳዲስ አንቴናዎች መግዛት አያስፈልግዎትም፡፡

[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]

**በዲቲቪዎች የሚተኩት የቀድሞ አናሎግ ቲቪዎች መጨረሻ ምንድን ነው? ሪሳይክል ማድረግ የሚቻልበት መንገድ አለ?**

አሮጌ አናሎግ ቲቪዎችን ወይም ሌሎች አሮጌ የኤሌክትሮኒክ ምርቶችን ማስወገድ ለሚሹ የተዘጋጁ ሪሳይክል የማድረጊያ ፕሮግራሞች አሉ (አናሎግ ቴሌቪዥኖች ከሽግግሩ በኋላም ማገልገል እንደሚችሉ ግን አይርሱ)፡፡ ከፕሮግራሞቹ አንዱ ማይግሪን ኤሌክትሮኒክስ የተሰኘው  ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም አማካኝነት ስለ አወጋገድ አማራጮችና በአቅራቢያዎ ስለሚገኙ ሪሳይክል የማድረግ ፕሮግራሞች ማወቅ ይችላሉ፡፡ ለተጨማሪ መረጃ http://www.mygreenelectronics.org ን ይጎብኙ፡፡

[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]

**በዲቲቪ ሽግግሩ የኬብል አገልግሎቶችን በሚጠቀሙ ቲቪዎች ላይ ተጽዕኖ አለው?**

የለውም የኬብል አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኛ ሲሆኑ የዲቲቪ ሽግግሩ ከኬብል አገልግሎቶች ጋር በተገናኙ ማናቸውም ቲቪዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር አይኖርበትም፡፡ የዲቲቪ ሽግግሩ የሚመመለከተው ባለ ሙሉ ኃይል ስርጭት የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ማለትም የሕዝብ የአገር ሞገዶችን በመጠቀም ፕሮግራሞቻቸውን ለተመልካቾች በመቀበያ አንቴና አማካኝነት የሚያስተላልፉ ጣቢያዎችን ነው፡፡

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**ኤፍሲሲ የኬብል ኩባንያዎች አገልግሎታቸውን ወደ ዲጂታል እንዲቀይሩ ያደርጋል?**

*አያደርግም፡፡ የኬብል ኩባንያዎች  አገልግሎታቸውን ወደ ዲጂታል መቀየር አያስፈልጋቸውም፡፡ የኬብል ኩባንያዎች አገልግሎታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ዲጂታል መቀየር የሚችሉ ቢሆንም አሁን የሚሰጡትን አናሎግ አገልግሎት እንዲቀይሩ አይደረግም፡፡ የኬብል ኩባንያዎች ማንኛውንም አናሎግ አገልግሎት እስከሰጡ ድረስ ከፌብሯሪ 17/2009 በኂላም ቢሆን አካባቢያዊ ስርጭታቸውን በአናሎግ መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ኤፍሲሲ ይጠይቃል፡፡*

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**የኬብል አገልግሎት የሚሰጠኝ ኩባንያ አሁን ያለ ሣጥን የምቀበላቸውን የኬብል ቻነሎች ለመቀበል ሣጥን እንዲኖረኝ ሊያደርግ ይችላል?**

*የተወሰኑ የኬብል ኩባንያዎች ወደ ዲጂታል አገልግሎት ሰጪነት ለመቀየር ወስነዋል፡፡ <u>ይህ በኬብል ኩባንያዎቹ የሚደረግ ንግድ ተኮር ውሳኔ እንጂ የፌዴራሉ መንግስት ያስቀመጠው ግዴታ አይደለም፡፡</u> አገልግሎት የሚሰጥ የኬብል ኩባንያ የተወሰኑ የኬብል ቻነሎቹን ከአናሎግ አገልግሎቱ ማዕቀፍ በማውጣት በዲጂታል አግልግሎ ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት አሊያም ሁሉንም አገልግሎቶቹን በአንድ ጊዜ ወደ ዲጂታል በመቀየር ለየትኛዎ ደንበኛ ምንም ዓይነት አናሎግ አገልግሎት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡ የኬብል ኩባንያዎት የሚያቀርባቸውን ቻነሎች በከፊል ወይም በሙሉ ወደ ዲጂታል አገልግሎት ማዕቀፍ ለማዛወር ከወሰነ ይህን የኬብል አገልግሎት ማግኘትዎን ለመቀጠል ‹‹ዲጂታል ኬብል›› መሣሪያ ማግኘት እንዲሚያስፈልግዎ ሊነግርዎ ይችላል፡፡ ይህም የዲጂታል ኬብል ሴት-ቶፕ ሳጥን መከራየትን ወይም መግዛትን አሊያም የ‹‹ኬብል ካርድ›› ማስገቢያ ያለውና ለዲጂታል ኬብል ዝግጁ የሆነ ቴሌቪዥን መግዛትን ሊያካትት ይችላል፡፡ የዲጂታል ኬብል መሣሪያው የምድር ለምድር የስርጭት ሞገዶችን ከዲጂታል ወደ አናሎግ ከሚቀይሩ ሳጥኖች የተለየ ነው፡፡*

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**ዲጂታል ፕሮግራሞችን ከኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ማግኘት ችዬ እንደሆን እንዴት አውቃለሁ?**

*የዲጂታል ወይም ኤችዲ ፓኬጆችን ከአቅራቢዎ ለማግኘት የደንበኝነት ስምምነት ካደርጉና ዲጂታል ፕሮግራሞቹን በዲጂታል ቴሌቪዥን የሚመለከቱ ከሆነ  ዲጂታል ፕሮግራሞችን ሊቀበሉ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ የዲጂታል ቲቪ ማዕቀፍ እና የሳተላይት ቲቪ አገልግሎት የግድ ዲቲቪ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ የእርስዎ የኬብል ወይም የሳተላይት ቲቪ ሲስተም ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም አናሎግ ፕሮግራሞችን በበለጠ ብቃት የሚያስተላልፍ ሲሆን ይችላል፡፡ ቅበላው የተሻሻለ ቢሆንም እንኳን አናሎግ ቴሌቪዥን ካለዎት ምናልባት ዲጂታል ሞገድ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ከኬብል ወይም ሳተለይት ቲቪ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር በመገናኘት መቀበል ስለሚችሏቸው ፕሮግራሞችና ለዚሁ ስለሚያስፈልጉት መሣሪያዎች ማወቅ ይችላሉ፡፡*

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**የኬብል አገልግሎት አቅራቢዬ የዲጂታል ኬብል ፓኬጅ ያቀርባል። ይህ ከኤችዲቲቪ ጋር ተመሣሣይ ነው?**

አይደለም። ‹‹ዲጂታል ኬብል›› እና በኬብል የሚተላለፍ ሀይ ዴፊኒሽን ፕሮግራም የተለያዩ ናቸው። የኤችዲቲቪ ፕሮግራሞችን በኬብል መከታተል ከፈለጉ የኬብል አቅራቢዎ ለሚሰጠው የኤችዲቲቪ ፓኬጅ ደንበኛ መሆንና ፕሮግራሞቹንም በኤችዲቲቪ መመልከት ያስፈልግዎታል። የኤች ዲቲቪ ፕሮግራሙን ለመመልከት የሴት-ቶፕ ሳጥን ወይም ሌላ መሣሪያ ሊያስፈልግዎት ይችላል።

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**እንደ ሲኤንኤን፣ ኤምኤስኤንቢሲ፣ ላይፍታይም ወዘተ ያሉ የኬብል ቲቪ ኔትወርኮች ወደ ዲጂታል ስርጭት መቀየር አለባቸው?**

የለባቸውም። የአሁኑ ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የሚደረግ ሽግግር የሚመለከተው የሕዝብ የአየር ሞገዶችን በመጠቀም ነጻ የምድር ለምድር ፕሮግራሞችን የሚያቀቡ ባለ ሙሉ ኃይል የቲቪ ጣቢያዎችን ነው። ሆኖም የኬብል አገልግሎት አቅራቢዎች ሲስተማቸውን ወደ ዲጂታል ስርጭቶች በሚቀይሩበት ወቅት ይህን ከስርጭት ውጭ የሆነ ፕሮግራማቸውን መቀበልዎን ለመቀጠል የዲጂታል ማዕቀፋቸው ደንበኛ መሆን ሊያስፈልግዎት ይችላል።

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**የምጠቀምበት የኬብል ሲስተም ፕሮግራሙን ወደ ዲጂታል ማዕቀፍ በማዛወሩ ምክንያት ለዲጂታል አገልግሎት ደንበኛ እንድሆን እገደዳለሁ?**

የእርስዎ የኬብል ሲስተም መቼ ፕሮግራሙን በዲጂታል ማዕቀፍ ስር እንደሚያደርግ እንዲሁም የሚያደርግ ወይም የማያደርግ መሆኑን ይወስናል። ይህም ዲጂታል መሣሪያ ያስፈልግዎታል ማለት ሲሆን ይችላል። ሆኖም የኬብል ስርዓትዎ ማንኛውንም አናሎግ አገልግሎት እስከሰጠ ድረስ በአካባቢዎ የሚገኙትን ጣቢያዎች በሙሉ በአናሎግ ፎርማት ማግኘትዎን ይቀጥላሉ።

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]*

**አናሎግ  ቲቪ ያላቸው  የኬብል አገልግሎት ደንበኞች ሴት-ቶፕ ሳጥንን ከኬብል ኩባንያቸው መግዛት ወይም መከራየት አለባቸው? ይህ ከሆነስ ዋጋው ምን ያህል ነው?**

የፌብሯሪ 17/2009 የሚያበቃው የደጂታል ቴሌቪዥን የሽግግር ቀን ገደብ የሚመለከተው ባለ  ሙሉ ኃይል የስርጭት ጣቢያዎችን ብቻ መሆኑ በቅድሚያ መታወቅ አለበት። የኬብል ኩባንያዎች ሲስተማቸውን ወደ ዲጂታል እንዲለወጡ በመንግስት  ያልተጠየቁ በመሆናቸው ቻነሎቻቸውን በአናሎግ ለደንበኞቻቸው ማቅረባቸውን መቀጠል ይችላሉ። የኬብል ኩባንያዎች ማናቸውንም አናሎግ አገልግሎት የሚያቀርቡ እስከሆነ ድረስ የአካባቢ ስርጭት ጣቢያዎቻቸውን በአናሎግ ለደንበኞቻቸው ማቅረባቸውን እንዲቀጥሉ በኤፍሲሲ ደንቦች ተደንግጓል። ይህ ግዴታ ከፌብሯሪ 17/2008  አንስቶ ቢያንስ ለሶስት ዓመታት ይቀጥላል። ግዴታው ከፌብሯሪ 17/2012 በኋላ ይቀጥል ወይስ አይቀጥል በሚለው ጉዳይ ላይ በ2011 ውሳኔ ይሰጣል። ይህም ማለት አናሎግ የኬብል አገልግሎትን የሚጠቀሙ ደንበኞች (ያለ ኬብል ሴት-ቶፕ ሳጥን) ይህ ማድረጋቸውን መቀጠል ይችላሉ።

ሆኖም ከንግድ ጋር ለተያያዙ ጉዳች ሲባል (ዲጂታል ከአናሎግ የተሻለ ብቃት ያለው በመሆኑ) የኬብል ኩባንያዎች ሲስተማቸውን ከአናሎግ አላላክ ወደ ዲጂታል ካደረገ (ማለትም ለደንበኞቹ የሚሰጣቸውን አናሎግ ቻነሎች ያቆማል) የአናሎግ ተጠቃሚ ደንበኞቹ የአካባቢያቸውን አናሎግ ጣቢያዎች መከታተላቸውን የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ማረጋገጥ አለበት፡፡

ይህም አናሎግ ቴሌቪዥን ያላቸው ደንበኞች የሴት-ቶኘ ሣጥን እንዲኖራቸው ይጠይቃል፡፡ የኬብል ኩባንያው ለደንበኛው የሴት-ቶኘ ሳጥን ካቀረበ ከዚህ ጋር የተያያዙ ማናቸውም ወጪዎች በኬብል ኩባንያው የሚወሰኑ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የአናሎግ ኬብል ደንበኞች ከኬብል ኩባንያቸው ጋር በመገናኘት የሴት-ቶኘ ሳጥን ያስፈልግ እንደሆን የሚያስፈልግበትን ጊዜ እና ክፍያ የሚጠይቅ መሆኑን እንዲጠይቁ ይመከራል፡፡

በተጨማሪም የኬብል ሴት-ቶኘ ሳጥን ከዲጂታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን የተለየ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ መሣሪያ አስፈላጊ የሚሆነው ምድር ለምድር የሚሰራጩ ፕሮግራሞችን በጣሪያ ላይ አንቴና ወይም በ‹‹ጥንቸል ጆሮ›› የውስጥ አንቴና አማካኝነት ለሚቀበሉ አናሎግ ቴሌቪዥኖች ነው፡፡ ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን እንደ ኬብል ወይም ሳተላይት ቲቪ አቅራቢዎች ላሉ የክፍያ ቴሌቪዥን አገልግሎት ጋር ለተገናኘ ቲቪ አስፈላጊ አይደለም፡፡ እንደ ኬብል ወይም ሳተላይት ላሉ የክፍያ አገልግሎቶች ስለሚያስፈልጉ ማናቸውም ሴት-ሳጥኖች መረጃዎችን ከ አገልግሎት አቅራቢው ማግኘት ያሻል፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

### የዲቲቪ ሽግግሩ ከሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ጋር በተገናኙ ቴሌቪዥኖች ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል?

የዲቲቪ ሽግግሩ የአካባቢያቸውን ቲቪ ጣቢያዎች በሳተላይት ሰሀኖቻቸው በሚቀበሉ የሳተላይት ደንበኞች ላይ ተጽዕኖ የለውም:: የሳተላይት ቲቪ አገልግሎት ዲጂታል አገልግሎት ሲሆን ሁሉም የሳተላይት ደንበኞች በሳተላይት የሚላኩ ፕሮግራሞችን ለመቀበል ከቲቪያቸው ጋር የሚገናኝ ሴት-ቶኘ ሳጥን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም በአገልግሎት ረገድ በሳተላይት ደንበኞች ላይ የሚከሰት ለውጥ መኖር የሌለበት ሲሆን ይህ የሚሆነው አካባቢያዊ የቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ አገልግሎታቸው በሳተላይት ተሸካሚ አማካኝነት የሚሰጡ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

## ቀያሪ ሳጥን

### የቀያሪ ሳጥን ኩፖን ፕሮግራም ምንድን ነው?

በዲቲቪ ሽግግር ወቅት ተጠቃሚዎችን ለመረዳት መንግስት የዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ኩፖን ፕሮግራምን አዘጋጅቷል፡፡ የንግድ ዲፓርትመንት  አካል የሆነው ብሔራዊ የቴሌኮምዩኒኬሽንስ እና መረጃ አስተዳደር (ኤንቲአይኤ) ፕሮግራሙን ይመራል፡፡ እያንዳንዱ በዩ.ኤስ. የሚገኝ ቤተሰብ ብቁ የሆኑ ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖችን ለመግዛት የሚችልባቸውንና እያንዳንዳቸው 40 ዶላር የሚያወጡ እስከ ሁለት የሚደርሱ ኩፖኖችን ማግኘት ይችላል፡፡ ኤንቲአይኤ ከጃንዋሪ 2008 ጀምሮ የኩፖን መጠየቂያ ማመልከቻዎችን መቀበል ጀምሯል፡፡ ኩፖኖቹ በተሳታፊ የደንበኞች ኤሌክትሮኒክስ ችርቻሮ ነጋዴዎች ዘንድ ለሚሰጡ ብቁ ቀያሪ ሳጥኖች ብቻ የሚያገለግሉት ሲሆን  በግዢ ወቅት ብቻ አገልግሎት ላይ መዋል ይኖርባቸዋል፡፡ (ኩፖኖቹ ከተላኩ ከ90 ቀናት በኋላ ዋጋቸውን እንደሚያጡ ልብ ይበሉ)፡፡ በአምራቾች ግምት መሠረት ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች እያንዳንዳቸው ከ40 እስከ 70 ዶላር ይሸጣሉ፡፡ ይህም የአንድ ጊዜ ወጪ ነው፡፡ በዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ዙሪያ ተጨማሪ መረጃዎችን ከwww.dtv2009.gov ድረ ገጽ ወይም በስ.ቁ. 1-888-388-2009 (የድምጽ ጥሪ) ወይም  በ 1-877-530-2634 (ቲቲዋይ) ደውለው ማግኘት ይችላሉ፡፡

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]()*

**ለኩፖን ብቁ የሆኑ ከዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች የትኞቹ ናቸው?**

ብሄራዊ የቴሌኮምዩኒኬሽን እና መረጃ አስተዳደር (ኤንቲአይኤ) የብቁ ሳጥኖችን ዝርዝር ከhttps://www.ntiadtv.gov/cecb_list.cfm ድረ ገጽ ማግኘት ይችላል፡፡

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]()*

**በአንድ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ላይ ከአንድ በላይ ቲቪ እና ቪዲዮ ሪከርደር ማገናኘት እችላለሁ?**

አናሎግ ብቻ የሆነ ጣቢያ መቀበያ ላለው እያንዳንዱ ቲቪ ወይም ሌላ መሣሪያ (ለምሣሌ ቪሲአር) አንድ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ያስፈልግዎታል፡፡ በመሠረቱ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን በአንድ መሣሪያ ውስጥ የሚገኝን አናሎግ ጣቢያ መቀበያ የሚተካ ነው፡፡ በመሆኑም አናሎግ ቲቪዎን እና ቪሲአርዎን አንድ ላይ መጠቀም ከፈለጉ (ለምሣሌ አንድን ፕሮግራም እየተከታተሉ ሌላ ፕሮግራምን ለመቅረጽ) ሁለት ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖችን መጠቀም ያስፈልግዎታል፡፡

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]()*

**ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች (የምድር ለምድር የቲቪ ስርጭቶችን ቀይረው በአናሎግ ቲቪ እንዲታዩ ማድረግ የሚችሉ) ዲጂታል ክሎዝድ ካፕሽኒንግን መቀየር ይችላሉ?**

አዎ፡፡ ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ቀያሪ ሳጥኖች የምድር ለምድር ዲጂታል ክሎዝድ ካፕሽኒንግን በአናሎግ ቲቪ ለማየት በሚያስችል መልኩ መቀየር የሚችሉ መሆን እንደሚኖርባቸው የኤፍሲሲ ደንቦች ይደነግጋሉ፡፡ http://www.fcc.gov/cgb/consumerfacts/dtvcaptions.htmlን ይመልከቱ፡፡

*[ወደ ጥያቄዎች ተመለስ]()*

**ከቴሌቪዥኔ ጋር በሁለት ሽቦዎች የተገናኘ የቀድሞ አንቴና አለኝ፡፡ በዚህ አንቴና አማካኝነት የመቀየሪያ ሳጥን መጠቀም እችላለሁ?**

አዎ፡፡ ሆኖም ሁለት አዳፕተሮች ያስፈልጉዎታል (‹‹ባሉንስ›› ወይም ‹‹አዛማጅ ትራንስፎርመሮች›› ተብለው በተጨማሪ የሚጠሩ ሲሆን ምስላቸው ከታች ተመልክቷል)፡፡ የአንቴናዎን ባለ ሁለት ሊድ ሽቦ ‹‹Antenna In›› ከሚለው የቲቪዎ መሰኪያ ላይ ፈትተው ያላቁ፡፡ ባለሁለት ሊድ የአንቴና ሽቦውን በባለሁለት ሊድ አዳፕተሩ ላይ ባሉት ተርሚናሎች ላይ ያያይዙ (ከታች በመጀመሪያም ምስል ላይ እንደተመለከተው) ከዚያም ባለሁለት ሊድ የአዳፕተሩን ኮአግዚያል ማገናኛ በቀያሪ ሳጥኑ ላይ ባለው ‹‹Antenna In (RF)›› የሚል መሰኪያ ላይ ያስገቡ፡፡ ኮአግዚያል ኬብሉን በመጠቀም አንደኛውን ጫፍ በቀያሪ ሳጥኑ ላይ በሚገኘው ‹‹Out To TV (RF)›› የሚል መሰኪያ ላይ ይሰኩ፡፡ ሌላኛውን ጫፍ በኮአግዚያል አዳፕተሩ ላይ ይሰኩት (ከታች ሁለተኛውን ምስል ይመልከቱ)፡፡





[ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ መሣሪያዎችን ማስተካከል (ከባለ ሁለት ሊድ የአንቴና ሽቦ ጋር እንደ መነሻ የሚያገለግል)]()

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

## አጠቃላይ ጥያቄዎች

**ተንቀሳቃሹን በባትሪ ኃይል የሚሰራውን ቴሌቪዥኔን ከፌብሯሪ 17/2009 ዘጠኝ በኋላ የቴሌቪዥን ስርጭትን ልከታተልበት እችላለሁ?**

ተንቀሳቃሽ የሆኑ በባትሪ የሚሰሩ አናሎግ ቴሌቪዥኖች ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ጋር ከተገናኙ ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ ምድር ለምድር የሚሰራጩ ፕሮግራሞችን ሊያሳዩ ይችላሉ። በአሁኑ ወቅት በባትሪ የሚሰሩ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች የሌሉ በመሆናቸው ውጫዊ የኃይል ምንጭ አስፈላጊ ይሆናል። በቅርብ የሚገኝ የዋና ኤልክትሪክ ኃይል ከሌለ ውጫዊ የባትሪ ኃይል ጣቢያ ወይም የድንገተኛ ጊዜ የኃይል ጄኔሬተር ለቀያሪ ሳጥን ኃይል ሊያቀርብ ይችላል።

በተጨማሪም ተንቀሳቃሽ በባትሪ የሚሰሩ ዲጂታል ቴሌቪዥኖች በገቢያ ላይ በመቅረብ ላይ ናቸው። በተንቀሳቃሹ ቴሌቪዥንዎት ላይ ‹‹Integrated Digital Tuner››፣ ‹‹Digital Tuner Built-in›› ‹‹Digital Receiver›› ወይም ‹‹Digital Tuner›› የሚል ሌብል ወይም ምልክት ካለ ዲጂታል ወደ አናሎግ መቀሪያ ሳጥን መጠቀም ሳያስፈልግዎት ዲጂታል የምድር ለምድር ስርጭቶችን መከታተል ይችላሉ።

እነዚህ መሣሪያዎች መኖራቸውንና ምርቶቹን የተመለከቱ መረጃዎችን ከኤሌክትሮኒስ ዕቃዎች ነጋዴ ማግኘት ይችላሉ።

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**በአናሎግ ቲቪዩ ላይ ያለው የኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ መስራቱን ይቀጥላል?**

የዲጂታል ቴሌቪዥን ሽግግሩ በኤኤም/ኤፍኤም የራዲዮ ስርጭት ላይ ተጽዕኖ ባይኖረውም በአናሎግ ቴሌቪዥኖች ውስጥ አብሮ የተሰራ ራዲዮ መሥራት አለመስራት እንደ መሣሪያው አይነትና እንዳደረጉት ማስተካከያ ይወሰናል።

<u>በራዲዮ/ቴሌቪዥን ማጣመሪያ ዩኒቱ ላይ የተገጠመ ዲጂታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን ከሌለ</u> በቴሌቪዥንዎ ውስጥ ያለው ራዲዮ እንደቀድሞው መሥራቱን ይቀጥላል።

<u>ከራዲዮ/ቴሌቪዥን ማጣመሪያ ክፍሉ ላይ የተገጠመ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን</u> ካለና ዩኒቱ የራዲዮ ሞገድን ለመቀበል በመቀሪያ ሳጥኑ ላይ የተገጠመውን ውጫዊ አንቴና የሚጠቀም ከሆነ የዲጂታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሳጥን አናሎግ ማሳለፍ የሚችል ከሆነ ራዲዮው የሚሰራ ይሆናል። አናሎግ ማሳለፍ የሚችሉ ሰሳጥኖችን ዝርዝር ከኤንቲአይኤ ድረ ገጽ www.ntiadtv.gov/cecb_list.cfm ማግኘት ይችላሉ (በኮከብ ምልክት የተወከለ)። ዩኒቱ ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ መሣሪያ ጋር ያልተገናኘ ከሆነም ራዲዮው የሚሠራ ይሆናል።

<u>የራዲዮ/ቴሌቪዥን ማጣመሪያ ዩኒቱ ከዲጂታል ወደ አናሎግ መቀየሪያ ሣጥን ጋር ያልተያያዘ አንቴናን ለኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ የሚጠቀም ከሆነ</u> ዩኒቱ ከዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ጋር ተያያዘም አልተያያዘም የኤኤም/ኤፍኤም ስርጭትን መቀበል መቻል ይኖርበታል።

[*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*]()

**ራዲዮኔ አሁኑ ወቅት የቲቪ ቻነሎችን የድምጽ ክፍል ይቀበላል። ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ መሥራቱን ይቀጥላል?**

አናሎግ የቴሌቪዥን ስርጭቶችን የድምጽ ክፍል ለመቀበል ዲዛይን የተደረጉ ራዲዮኖች የዲጂታል ቲቪ ስርጭቶችን የድምጽ ክፍል መቀበል አይችሉም። የዲጂታል ቴሌቪዥን ስርጭቶችን የድምጽ ክፍል መቀበል የሚችሉ ዲጂታል ቴሌቪዥኖች ወይም ራዲዮኖች ለገበያ ሲቀርቡ ማግኘት ይችላሉ።

**በአካባቢዬ የሚገኘው የኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ ጣቢያ የቲቪ ቻነልን የድምጽ ክፍል መልሶ ያሰራጫል። የራዲዮ ጣቢያው ይህን አገልግሎቱን ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ ይቀጥላል?**

የዲጂታል ቴሌቪዥን የድምጽና ምስል ሞገድ የተዋሀደ በመሆኑ የቲቪ ጣቢያን የድምጽ ክፍል መልሶ የሚያሰራጭ አንድ የኤኤም/ኤፍኤም ጣቢያ ይህን አገልግሎቱን ለመቀጠል ተጨማሪ መሣሪያ መግጠም ይኖርበታል። በአካባቢዎ የሚገኘው የኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ ጣቢያ የቲቪ ቻነልን ድምጽ ማሠራጨቱን ይቀጥል እንደሆን ለማወቅ አሠራጩን ይጠይቁ።

[*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*]()

**በአካባቢዬ የሚገኝ የቴሌቪዥን ጣቢያ የኤኤም/ኤፍኤም ራዲዮ ጣቢያዎችን በቴሌቪዥን ቻነል መልሶ ያስተላልፋል። ከፌብሯሪ 17/2009 በኋላ እነዚህን ተመልሰው የሚሰራጩ የራዲዮ ሥርጭቶች በቴሌቪዥኔ ማድመጥ እችላለሁ?**

በአካባቢው የሚገኘው የቴሌቪዥን ጣቢያ የራዲዮ ስርጭቶችን በሙሉ ኃይል የቴሌቪዥን ጣቢያ ቻነል መልሶ የሚያሰራጭ ከሆነ የዚያን ቴሌቪዥን ቻናል ለመከታተልና ማንኛውንም ተዛማጅ ድምጽ በአናሎግ ቴሌቪዥን ለመስማት ደጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ያስፈልግዎታል።

[*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*]()

**ዲጂታል የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያዎችን መስጠታቸውን ይቀጥላሉ?**

አዎ። ዲጂታል ቴሌቪዥን ጣቢያዎች የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት (ኢኤኤስ) መተግበራቸውን መቀጠል ይጠበቅባቸዋል። ስለ ኢኤኤስ ተጨማሪ መረጃዎችን ከ[www.fcc.gov/cgb/consumerfacts/eas.html](www.fcc.gov/cgb/consumerfacts/eas.html) ድረ ገጽ ማግኘት ይችላሉ።

[*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*]()

**የአነስተኛ ኃይል (ኤልፒቲቪ)፣ ምድብ ሀ እና ቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያዎች ምንድን ናቸው? የዲቲቪ ሽግግር ተጽዕኖ የሚያሳድርባቸው በምን መልኩ ነው?**

ኮንግረሱ ‹‹ባለ ሙሉ አቅም›› የቲቪ ጣቢያዎች ከፌብሯሪ 17/2009 ጀምሮ በአናሎግ ማሠራጨት እንደማይችሉ ትዕዛዝ አስተላልፏል። አብዛኞቹ ለእይታ የሚበቁ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ባለሙሉ ኃይል ጣቢያዎች ቢሆኑም ሶስት የቴሌቪዥን ጣቢያ ምድቦች አሉ ‹‹የአነስተኛ ኃይል›› ጣቢያዎች ‹‹ክፍልሀ›› ጣቢያዎች እና ‹‹ቲቪ ትራንስሌተር›› ጣቢያዎች። በአሁኑ ወቅት እነዚህ ጣቢያዎች ሥርጭታቸውን ወደ ዲጂታል ስርጭት እንዲቀይሩ የተቀመጠላቸው ቀነ ገደብ የለም።

ለአነስተኛ ማኅበረሰቦች አካባቢያዊ የቴሌቪዥን አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን ዕድል ለመፍጠር ኤፍሲሲ በ1982 ዓ.ም. የአነስተኛ ኃይል ቴሌቪዥን (ኤልፒቲቪ) አገልግሎትን መሠረተ። እነዚህ ማኅበረሰቦች በገጠር አካባቢዎች ውስጥ ሊገኙ ወይም በትልቅ የከተማ አካባቢዎች ውስጥ ያሉ ማኅበረሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ። ኤልፒቲቪ ጣቢያዎች በተለያዩ ቡድኖችና ድርጅቶች ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ

ሲሆን ከነዚህ መካከል ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ አብያተ ክርስቲያናትና የኃይማኖት ቡድኖች፣ የአካባቢ መንግስታት ትልቅና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች ይገኙበታል። ከ2100 በላይ ፈቃድ የተሰጣቸው ኤልፒቲቪ ጣቢያዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው። ከኤልፒቲቪ ፕሮግራሞች መካከል በሳተላይት የሚላኩ ፕሮግራሞች አገልግሎት ሲንዲኬትድ ፕሮግራሞች ፊልሞች እንዲሁም በርካታ በአካባቢ ደረጃ የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ይገኙበታል።

ምድብ ሀ ቲቪ ጣቢያዎች የሚባሉት ቀድሞ ኤልፒቲቪ የነበሩና ለኤልፒቲቪ ጣቢያዎች ያልተሰጡ የተወሰኑ የጣልቃ ገብነት ጥበቃ መብቶች ያላቸው ናቸው። እነዚህ ጣቢያዎች ከቴክኒክ አንጻር ከኤልፒቲቪ ጣቢያዎች ጋር ተመሣሣይ በሆኑም ከኤልፒቲቪ ጣቢያዎች በሚለይ መልኩ ቢያንስ በሳምንት ለሶስት ሰዓታት በአካባቢው የተዘጋጀ ፕሮግራምን ማሠራጨትና ሙሉ ኃይል ያላቸውን ጣቢያዎች ከሚመለከቱና ቴክኒካዊ ያልሆኑ መመሪያዎችን መከተል አለባቸው። 600 ያህል ፈቃ የተሰጣቸው ምድብ ሀ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በሥራ ላይ ናቸው።

ቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያ የባለ ሙሉ ኃይል ቲቪ ማሰራጫ ጣቢያን ፕሮግራሞች መልሶ ያሰራጫል። የትራንስሌተር  ጣቢያዎች  ዋነኛ ተግባር ከሙሉ ኃይል የቲቪ ጣቢያዎች በጣም ርቀው በመገኘታቸው አሊያም በመልክዓ ምድር (ለምሣሌ ወጣ ገባ የሆነ አቀማመጥ ወይም ተራሮች ያሉበት ስፍራ) ምክንያት ምድር ለምድር የሚስረጩ ነጻ ቲቪ ጣቢያዎችን ሞገድ መቀበል የማይችሉ ማህበረሰቦችን ማገልገል ነው። ፈቃድ ከተሰጣቸው 4700 ቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያዎች ውስጥ አብዛኞቹ ለአገሪቱ ተራራማ ወይም ሩቅ አካባቢዎች አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

በምድር ለምድር ሥርጭት የሚመለከቷቸው የስርጭት ጣቢያዎች (በጣሪያ ላይ አንቴና ወይም በ‹‹ጥንቸል ጆሮ›› አንቴና አማካኝነት) ኤልፒቲቪ ምድብ ሀ ወይም ቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያዎች መሆናቸውን የሚለዩባቸው በርካታ መንገዶች አሉ። ምድብ ሀ ጣቢያዎች በእይታ ወይም በድምጽ አማካኝነት ፈቃድ ከወሰዱባቸው ማኅበረሰባት ጋር እንዲያገናኙ እንዲሁም ስርጭት በሚጀምረባቸው በሚያበቁባቸውና በየሰዓቱ የጣቢያ መለያቸውን እንዲያሳዩ (ለምድብ ሀ የ‹‹-ሲኤ›› ቅጥያ ያለበትን) ይጠበቃል። በተጨማሪም የኤልፒቲቪ ጣቢያዎች በመደበኛነት የጣቢያቸውን መለያ ምልክት መለየት አለባቸው። በአካባቢው የተሠራ ፕሮግራም  ሲሰራጭ መለያ ምልክታቸውን እና ፈቃድ የወሰዱበትን ማህበረሰብ በስርጭት መጀመሪያ ማብቂያና በየሰዓቱ መግለጽ አለባቸው የኤልፒቲቪ መለያ ምልክቶች ‹‹-ኤልፒ›› የሚል የመድረሻ ቅጥያ ያላቸውን አራት ፊደላት አሊያም እንደ አማራጭነት በኬ ወይም በደብልዩፊደል የሚጀምሩና ሁለት ቁጥሮችን (የሚያስራጩባቸውን ቻነሎች) እና ሁለት ተጨማሪ ፊደላትን የሚያስከትሉ አምስት ፊደላትን ወይም አኃዞችን ሊይዙ ይችላሉ። በተጨማሪም ጥቂት ቲቪ ትራንስሌተሮች ሞገዶቻቸውን መልሰው በሚያስራጩላቸው ባለ ሙሉ ኃይል ቲቪ ጣቢያዎች ሊለዩ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ኤልፒቲቪ ምድብ ሀ እና ቲቪ ትራንስሌተር  ጣቢያዎች የራሳቸውን ሁኔታ የተመለከቱ መረጃዎችን በመደበኛነት ሊያሰራጩና የዲቲቪ ሽግግርን የተመለከተ መረጃን ሊያካትቱ ይችላሉ።

የፌብሯሪ 17/2009 የአናሎግ ስርጭት ማብቂያ ጊዜ የዝቅተኛ ኃይል ምድብ ሀ እና የቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያዎችን የማይመለከት ቢሆንም ከሆነ ጊዜ በኋላ እነዚህም ጣቢያዎች ስርጭታቸውን ወደ ዲጂታል እንደቀይሩ ኤፍሲሲ የሚያስገድድ ይሆናል። ከነዚህ ጣቢያዎች ውስጥ 2000 ያህሉ የዲጂታል አገልግሎት መስጫዎችን እንዲገነቡ ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን ጥቂቶቹ ከወዲሁ በዲጂታል ማሰራጨት ጀምረዋል። ኤፍሲሲ በአሁኑ ወቅት ከዝቅተኛ ኃይል ዲጂታል ሽግግር ጋር የተያያዙ ቀሪ ጉዳዮችን እያጤነ ሲሆን እነዚህን ጣቢያዎች በተመለከተ ለወደፊት ውሳኔዎችን የሚሰጥ ይሆናል።

ነጻ የምድር ለምድር ፕሮግራምን የሚቀበል አናሎግ ብቻ የሆነ ቴሌቪዥን ካለዎት (የጣሪያ ላይ አንቴና ወይም ‹‹የጥንቸል ጆሮ›› የመሰለ በቲቪው ላይ የሚቀመጥ አንቴና ያለው)፤ ዲጂታል የቴሌቪዥን ሥርጭትን ለመቀበል ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሣጥን መግዛት ያስፈልግዎታል። እያንዳንዱ በዩ.ኤስ. የሚገኝ ቤተሰብ ብቁ የሆኑ ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖችን መግዛት ይችል ዘንድ እያንዳንዳቸው 40 ዶላር ዋጋ ያላቸውንና እስከ ሁለት የሚደርሱ ኩፖኖችን ማግኘት ይችላል።  የንግድ ዲፖርትመንት አካል የሆነው ብሔራዊ የቴሌከምዩኒኬሽን እና መረጃ አስተዳደር (ኤንቲአይኤ) ይህን ፕሮግራም ይመራል። (ኩፖኖቹ ከተላኩ ከ90 ቀናት በኋላ ዋጋቸውን እንደሚያጡ ልብ ይበሉ)። ተጨማሪ

መረጃዎችን ከ www.dtv2009.gov ድረ ገጽ ማግኘት ወይም በስ.ቁ. 1-888-388-2009 (የድምጽ ጥሪ) 1-877-530-2634 (ቲቲዋይ) ደውለው ማግኘት ይችላሉ፡፡

ዲጂታል ስርጭቶችን በአናሎግ ቴሌቪዥን ለመከታተል ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ከገዙና አናሎግ ኤልፒቲቪ ምድብ ሀ ወይም ቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያዎችን መከታተል ምንም መቀጠል ከፈለጉ ‹‹አናሎግ የማሳለፍ›› አቅም ያለው ቀያሪ ሣጥን መግዛት ይኖርብዎታል፡፡ ሣጥኑ የአናሎግ ስርጭት ሞገዶችን በቀያሪው ሣጥን ውስጥ አልፈው በአናሎግ ቲቪዎ ጣቢያ መቀበያ ውስጥ እንደገቡ ያደርጋል፡፡ የኤንቲአይኤ የቲቪ ቀያሪ ሣጥን ኩፖን ፕሮግራም አናሎግ የማሳለፍ ችሎታ ያላቸው ስርቲ ፋይድ ቀያሪ ሳጥን ሞዴሎች አሉት ወቅታዊ ብቁ የሆኑ ቀያሪ ሣጥኖችን ዝርዝር ከhttps://www.ntiadtv.gov/cecb_list.cfm ማግኘት ይቻላል፡፡ አናሎግ የማሳለፍ ችሎታ ያላቸው የቀያሪ ሣጥን ሞዴሎች በዝርዝሩ ላይ ከአጠገባቸው የኮከብ ምልክት ተደርጎባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ኤንቲአይኤ ብቁ የሆኑ ቀያሪ ሣጥኖችን ወቅታዊ ዝርዝር አናሎግ የማሳለፍ ችሎታ ባላቸው ላይ የኮከብ ምልክት በማድረግ የቀያሪ ሣጥን ኩፖኖችን ለሚቀበል እያዳንዱ ቤተሰብ ይልካል፡፡ በተጨማሪም የሚገዙት ቀያሪ ሣጥን አናሎግ የማሳለፍ ችሎታ ይኖረው እንደሆን ከሻጩ ጠይቀው ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

አናሎግ የማሳለፍ ችሎታ የሌለው ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሣጥን ከገዙና የአናሎግ ቲቪ ስርጭቶችን መመልከት ከፈለጉ፤ ሣጥኑን ማለፍ የሚችል የአንቴና ማብሪያ ማጥፊያ/ስዊች/ ወይም የሲግናል ‹‹ስፕሊተር›› ማገናኘት ሊኖርብዎ ይችላል፡፡ ከአናሎግና ከዲጂታል ጣቢያዎች የሚተላለፉ ስርጭቶችን ለመከታተል በሚያስችል መልኩ እንዴት ሣኑን ማገናኘት እንዳለብዎ የሚገልጹ መመሪያዎችን ዲጂታል-ወደ-አናሎግ ቀያሪ ሣጥኑን ካመረተው ውይም ከሸጠልዎ አካል ማግኘት ይችላሉ፡፡

የኤልቲቪ፣ ምድብ ሀ እና ቲቪ ተርጓሚ ጣቢያዎች ሥርጭታቸውን ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የመቀየር ዕቅድ ይኖራቸው እንደሆን ለማወቅ ተመልካቾች መረጃዎችን ከነዚሁ ቦታዎች መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ተመልካቾች ስለ አነስተኛ ኃይል፣ ምድብ ሀ እና ቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያዎች ዲጂታል ሽግግር ማናቸውንም ወቅታዊ መረጃዎች ከwww.fcc.gov ድረ ገጽ ማግኘት ይችላሉ፡፡

የሁሉም ምድብ ሀ፣ ኤልፒቲቪ እና ቲቪ ትራንስሌተር ጣቢያዎች ዝርዝር፡- Excel

*የአነስተኛ ኃይል ቴሌቪዥን ጣቢያ ፍለጋ መሣሪያ*

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**ከዲጂታል ሽግግሩ በኋላ ከኤልፒቲቪ ወይም ከትራንስሌተር ጣቢያዎች የምድር ለምድር አናሎግ የቲቪ ሥርጭቶችን ለመከታተል ያሉኝ አማራጮች ምንድን ናቸው?**

በአንቴና አማካኝነት የሚገኙ የአናሎግ የኤልቲቪ እና የትራንስሌተር ጣቢያዎችን ስርጭት ለመከታተል ከሚከተሉት ርምጃዎች አንድ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑትን ይተግብሩ፡-

- አናሎግ ቲቪን ከስርጭት መቀበያ አንቴና ጋር እንደተገናኘ በመተው አናሎግ የኤልፒቲቪ እና የተርጓሚ ጣቢያዎችን ስርጭት መከታተል፡፡
- አናሎግ የማሳለፍ ችሎታ ያለው ዲጂታል ውድ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን መግዛት ለቲቪ ቀያሪ ሳጥን ኩፖን ፕሮግራም ብቁ ስለመሆናቸው በኤንቲአይኤ ማረጋገጥ የተሰጣቸውን ዲጂታል ውድ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች ወቅታዊ ዝርዝር ለማግኘት በhttps://www.ntiadtv.gov/cecb_list.cfm ላይ ክሊክ በማድረግ ከአጠገባቸው የኮከብ (*) ምልክት የተደረገባቸውን ሳጥኖች ይፈልጉ፡፡ አናሎግ የማሳለፍ ገጽታ የአናሎግ ቲቪ ስርጭቶችንና የዲጂታል ቲቪ ስርጭቶችን በቀያሪ ሳጥን አማኝነት እንዲከታተሉ ያስችልዎታል፡፡

- አናሎግ የሚያሳልፍ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥን ይግዙና ‹‹ስፐሊተር›› ወይም የአንቴና መቀያየሪያ ማብሪያና ማጥፊያን በማገናኘት አናሎግና ዲጂታል ስርጭቶችን ይቀበሉ፡፡ ከአናሎግና ከዲጂታል ጣቢያዎች የሚተለፉ ስርጭቶችን ለመከታተል በሚያስችል መልኩ ሳጥኑን እንዴት ማገናኘት እንዳለብዎ የሚገልጹ መመሪያዎችን ከተጠቃሚ የኤሌክትሮኒክስ ሻጩ ያግኙ፡፡
- ዲጂታል ቴሌቪዥን ይግዙ አብሮ የተሰራ ዲጂታል ጣቢያ መቀበያ ያለው ቴሌቪዥን ሁለቱንም አናሎግና ዲጂታል ፕሮግራሞችን እንዲሁም የኤልፒቲቪ እና ተርጓሚ ጣቢያዎች በአናሎግ ማስራጮቻቸውን እስከ ቀጠሉ ድረስ የእነዚህኑ አናሎግ ስርጭት ለመከታተል ይችላሉ፡፡
- ለመከታተል የሚፈልጉትን (የሚፈልጓቸውን) አናሎግ ጣቢያ (ዎች) የሚያቀርብ የኬብል ቴሌቪዥን ወይም ሌላ የክፍያ አገልግሎት ደንበኛ ይሁኑ፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**እንደ  ቪ-ቺፕ ያሉ የወላጅ መቆጣጠሪያዎችን አሁን በአናሎግ ቲቪዬ ላይ እንደምጠቀመው  ሁሉ በዲጂታል ቲቪም መጠቀም እችላለሁ?**

አዎ፡፡ የቪ-ቺፕ ቴክኖሎጂ ወላጆች የአንድን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ደረጃ አሰጣጥ (ሬቲንግ) መሠረት በማድረግ  ፕሮግራሙን የሚያገኙበት ስልት ነው፡፡ ደረጃዎቹ በቴሌቪዥን ሲግናሉ ውስጥ ኢንኮድ የተደረጉ ናቸው፡፡ ቪ-ቺፕ የእያንዳንዱን ፕሮግራም ኢንኮድ የተደረገ ደረጃ በማንበብ በወላጆች የእገዳ ምርጫ መሠረት ትርዒቶችን ያግዳል፡፡ በኤፍሲሲ ደንቦች መሠረት ቪ-ቺፖች  እንደ አናሎግ ቴሌቪዥኖች ሁሉ በዲጂታል ቴሌቪዥኖችና በሌሎች የዲቲቪ መቀበያ መሣሪያዎች ውስጥ አብረው መሠራት አለባቸው፡፡ ‹‹የቲቪ የወላጅ መመሪያዎች›› ተብለው በተጨማሪነት ስለሚታወቁት የደረጃ (ሬቲንግ) ስርጭቶች ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት ይችላሉ፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**በዲጂታል ቴሌቪዥኔ ላይ የምመለከተው ምስል የቲቪውን ስክሪን ሙሉ በሙሉ የማይሸፍ ነው ለምንድን ነው?**

የተለመደው አናሎግ ቲቪ የ4፡3 መጠን አለው (ለስኩዌር በጣም ይቀርባል)፡፡ ይህም ማለት ለእያንዳንዱ 4 ኢንች የስክሪን ስፋት 3 ኢንች ተጓዳኝ ቁመት ይኖረዋል፡፡ አብዛኞቹ ዲጂታል ቴሌቪዥኖች የ16፡9 ምጣኔ (ሬክታንጉላር) ያላቸው ሲሆን ‹‹ዋይድ ስክሪን›› ተብለው ይጠራሉ፡፡ የ16፡9 ምጣኔ ከፊልሞች ገጽታ ጋር ተቀራራቢ ሲሆን በ16፡9 ምጣኔ የሚቀርቡ የቴሌቪዥን ፕሮግራም መጠን እያደረገ መጥቷል፡፡

የቴሌቪዥን ፕሮግራሙ የምስል ምጣኔ እና የቴሌቪዥንዎ ስክሪን ምጣኔ ሳይጣጣም ሲቀር የምስሉ ገጽታ እንዳይበላሽ ሲባል በምስሉ አናት እና/ወይም ጎኖች ላይ ጥቁር መስመሮች ሊታዩ ይችላሉ፡፡

4፡3 በሆነ ቴሌቪዥን ላይ የ16፡9 መጠን ያለውን ምስል  ለማሳየት ዲጂታል ቴሌቪዥንዎ ወይም ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥንዎ  በምስሉ አናት እና ግርጌ ላይ ጥቁር መስመሮችን ሊያኖር ይችላል ይህ ሂደት ‹‹ሌተርቦክሲንግ›› ይባላል፡፡

በተመሣሣይም 4፡3 የሆነ ምስልን በ16፡9 የቴሌቪዥን ስክሪን በአግባቡ ለማሳየት በስክሪኑ ጎኖች ላይ መስመሮች እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡ ይህ  ሂደት ‹‹ፒላርቦክሲንግ›› ይባላል፡፡

በተጨማሪም የተወሰኑ ፕሮግራሞች በስርጭት ወቅት ‹‹ሌተርቦክስ›› ወይም ‹‹ፒላርቦክስ›› ሊደረጉ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ባርካታ ማስታወቂያዎች በአናሎግ በ4፡3 ምጣኔ የሚዘጋጁ ቢሆንም ‹‹ዘመናዊ›› ገጽታን እንደለበሱ ወይም ለጽሑፍ ወይም ሰብታይትል ቦታ ለመተው ሲባል በሌተርቦክስ ይሠራጫሉ፡፡ እንደዚህ  ዓይነቱ ማስታወቂያ በዋይድስክሪን (16፡9) ፕሮግራም ወቅት ሲተላለፍ ፒላርቦክስ ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ ከላይና ከታች መስመሮች ያሉት ባለ 16፡9 ፎርማት ስርጭት ያስከትላል፡፡ ይህ ስርጭት በባለ 16፡9 ቴሌቪዥን ላይ ሲታይ ከላይ ከታችና ከሁለቱም ሳጥኖች ጥቁር መስመር ያለበትን ምስል ይፈጥራል፡፡ ይህ ክስተት ‹‹ፖስቴጅ ስታምፕ›› ይባላል፡፡

በርካታ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖች  እነዚህ መስመሮች ማጥፋት ይችሉ ዘንድ ምስሉን ‹‹ማቅረብ›› ያስችሉዎታል፡፡ ይህ ሁኔታ የተወሰው የምስሉ ክፍል እንዲቆረጥ ያደርገዋል፡፧ በተጨማሪም አንዳንድ ዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥኖችና ዲጂታል ቴሌቪዥኖች ምስሉን ‹‹በመለጠጥ›› ወይም ‹‹በመደፍጠጥ›› ስክሪኑ እንዲሞላ ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ በማቅረብና በመለጠጥ ወይም በመደፍጠጥ (በስክሪንዎት ላይ ያለውን ምስል) መስመሮች እንዴት ማጥፋት እንደሚችሉ ለማወቅ እባክዎ የዲጂታል ቴሌቪዥንዎን ወይም የዲጂታል ወደ አናሎግ ቀያሪ ሳጥንዎን የአጠቃቀም መመሪያ ያንብቡ፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**አንዳንድ በዲጂታል ቴሌቭዥኔ የምመለከታቸው ፕሮግራሞች ከሌሎች ይበልጥ ‹‹ጥራት ያላቸው›› ለምንድን ነው?**

እንደ ቴሌቭዥንዎ ዓይነት የምስሉ ምስል ከፕሮግራሞች ጋር ሲቀያየር ሊያስተውሉ ይችላሉ፡፡ ከፍተኛ ሪዞሉሽን ባላቸው ቴሌቪዥኖች ላይ ዝቅተኛ ሪዞሉሽን ያላቸው ቻነሎች ወይም ፕሮግራሞች ሲታዩ በየራሳቸው ዝቅተኛ ሪዞሉሽን ይታያሉ፡፡ በመሆኑም በከፍተኛ ሪዞሉሽን ከሚሰራጭ ቻነል ወይም ፕሮግራም ወደ ዝቅተኛ ሪዞሉሽን ወዳለው ቻነል ወይም ፕሮግራም የመቀየሩ ሂደት የምስል ጥራ መቀነስን ያስከትላል፡፡

ማሰራጫዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸው ሪዞሉሽኖች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

| | |
|---|---|
| **ስታንዳርድ ዴፊኒሽን ቲቪ (ኤስዲቲቪ)** - ኤስዲቲቪ ለአናሎግም ሆነ ለዲጂታል ቲቪ መሠረታዊ የጥራትና የማሳያ ደረጃ ነው፡፡ የኤስዲቲቪ ሥርጭት ተለምዷዊው (4:3) ወይም ዋይድስክሪን (16:9) የመጠን ፎርማት ሊሆን የሚችል ሲሆን፧ 480 ኢንተርሌስድ የሪዞሉሽን መስመሮች ይጠቀማል፡፡ | SDTV STANDARD DEFINITION TELEVISION |
| **ኢንሀንስድ ዴፊኒሽን ቲቪ (ኢዲቲቪ)** - ኢዲቲቪ ከአናሎግ ቴሌቪዥንና ከስታንዳርድ ዴፊኒሽን ዲጂታል ቴሌቪዥን የተሻሻለ ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ኢዲቲቪ በዋይድስክሪን (16:9) ወይም በተለምዷዊው (4:3) የመጠን ፎርማት ሊቀርብ የሚችል ሲሆን 480 በቅደም ተከተል ስካን የሚደረጉ መስመሮችን የሚጠቀም ነው፡፡  ይህም የኤስዲቲቪ ሪዞሉሽን እጥፍ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ዲቪዲዎች የሚገኝ ሪዞሉሽን ነው፡፡ | EDTV ENHANCED DEFINITION TELEVISION |
| **ሀይ ዴፊኒሽን ቲቪ (ኤችዲቲቪ)** - በዋይድስክሪን ፎርማት (16:9) የሚቀርበው ይህ ኤችዲቲቪ ከሁሉም ዲጂታል ሥርጭት ፎርማቶች የላቀ ሪዞሉሽንና የምስል ጥራት ያለው ነው፡፡ 1080 ኢንተርሌስድ ወይም 720 በቅደም ተከተል ስካን የሚደረጉ የሪዞሉሽን መስመሮችን የያዘና ዲጂታል ሳራውንድ ድምጽን ለማሠራጨት የሚያስችል ነው፡፡ | HDTV HIGH-DEFINITION TELEVISION |

ለተጨማሪ መረጃ www.dtv.gov/DTV_booklet.pdf ድረ ገጽን ይጎብኙ፡፡

*ወደ ጥያቄዎች ተመለስ*

**ለመጨረሻ ጊዜ የተከለሠበት/ወቅታዊ የተደረገበት ቀን** 09/11/08